የWASHINGTON ግዛት
የአስተዳደራዊ ችሎቶች ቢሮ
የሥራ አጥነት ኢንሹራንስ ይግባኝ

# ለስራ አጥነት ችሎትዎ እንዴት እንደሚዘጋጁ

ጥያቄዎች አሉዎት?
የቃል አስተርጓሚ ይፈልጋሉ?
ወደ (800) 366-0955 ይደውሉ

***የእኔን ይግባኝ ማን ሰምቶ ይወስናል?***
አንድ ሰው ወይም ንግድ በሥራ ቅጥር ደህንነት መምሪያ (Employment Security Department, ESD) በተሰጠው ውሳኔ ካልተስማማ፣ የአስተዳደራዊ ችሎቶች ቢሮ (Office of Administrative Hearings, OAH) ክርክሩን ሰምቶ ይወስናል። የእርስዎን ጉዳይ የሚሰማው ዳኛ ገለልተኛ ሲሆን በESD የተቀጠረ አይደለም።

***ችሎቴን እንዴት እከታተላለሁ?***
በስልክ። ለመሳተፍ መደወል አለብዎ።
በችሎት ማስታወቂያ ውስጥ ያሉትን መመሪያዎች ይከተሉ።

***የቃል አስተርጓሚ ብፈልግስ?***
ችሎቶች እና ውሳኔዎች በእንግሊዝኛ ናቸው። እርስዎ ወይም ማንኛቸውም ምስክሮችዎ የቃል አስተርጓሚ ከፈለጉ፣ እባክዎ በተቻለ ፍጥነት OAHን (800) 366-0955 ላይ ያነጋግሩ። ጓደኞች እና የቤተሰብ አባላት ለአንድ ፓርቲ ወይም ለምስክር ማስተርጎም አይችሉም።

***ለአካል ጉዳተኛ የሚደረግ ማስተካከያ ካስፈለገኝስ?***
ማስተካከያ ከፈለጉ፣ እባክዎ በተቻለ ፍጥነት OAHን (800) 366-0955 ላይ ያነጋግሩ።

***የችሎት ቀጠሮዬን ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍ ካስፈለገኝስ?***
ችሎት የሚሰማበትን ቀን ወይም ሰዓት መቀየር ከፈለጉ በተቻለ ፍጥነት **(800) 366-0955** ላይ ወደ OAH ይደውሉ።
ዳኛ ጥያቄዎን ይገመግሙታል። ዳኛው የችሎቱ ቀን እንዲለወጥ ለምን እንደፈለጉ ሊጠይቁዎት ይችላሉ።
ዳኛው የችሎቱ ቀን እንዲቀየር ለምን እንደፈለጉ ሊጠይቁዎት ይችላሉ። ቀን ወይም ሰዓቱ ሊለወጥ ይችል እንደሆነ ዳኛው ይወስናሉ። ቀኑ እንደተለወጠ ካልተነገረዎት በስተቀር አሁንም መገኘት እና ለችሎትዎ መዘጋጀት ይኖርብዎታል።

***ከእንግዲህ ይግባኝ ማለት ባልፈልግስ?***
ከአሁን በኋላ ችሎት የማያስፈልግዎት ከሆነ ይግባኝዎን መሰረዝ ይችላሉ። ይግባኝዎን ለመሰረዝ ለOAH ይጻፉ ወይም ይደውሉ፣ ወይም በችሎትዎ ላይ ለዳኛው ይንገሩ። ይግባኝዎን ከሰረዙ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ የESD ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል። ወደፊት ይግባኝ ማለት አይችሉም። ይግባኝዎን እንዲሰረዝ በዚህ አድራሻ በመስመር ላይ መጠየቅ ይችላሉ፦
oah.wa.gov/Content-Area-Management/Forms-Hub/Withdrawal-Unemployment-Insurance

***ለችሎቱ መዘጋጀት***
የእርስዎ መብቶች በዚህ ይግባኝ ላይ ጥያቄ ውስጥ ናቸው። ጉዳይዎን ለዳኛው የማቅረብ ሃላፊነት አለብዎት። መዘጋጀት ያስፈልግዎታል።

1. የችሎት ማስታወቂያውን ያንብቡ
2. መገኘትዎን እንዳይረሱ የችሎቱን ቀን እና ሰዓት በማስታወሻ ይያዙ።
3. የኤግዚቢት ጥቅልን በጥንቃቄ ያንብቡ። ኤግዚቢቶች ከጉዳይዎ እውነታዎች ጋር የተያያዙ ሰነዶች ናቸው። በችሎት ጥቅልዎ ውስጥ ከስምንት እስከ አስር በሚደርሱ ገፆች ይግባኝ በጠየቁት የውሳኔ ደብዳቤ ይጀምራሉ እና እስከ ጥቅሉ መጨረሻ ድረስ ይሄዳሉ።
   **በችሎቱ ወቅት እነዚህ ሰነዶች ከእርስዎ ጋር መሆናቸውን ያረጋግጡ።**
4. ዳኛው ስለ ጉዳዩ ጠቃሚ እውነታዎችን እንዲገነዘብ የሚያግዙ ተጨማሪ ሰነዶች አሉዎት? ካሉዎት፣ ከዚህ በታች “ሰነዶችን ማስገባት” ላይ ያሉትን መመሪያዎችን ይመልከቱ።
5. በችሎትዎ ላይ ምስክሮችን ማምጣት ይችላሉ። ምስክር ማለት ዳኛው እንዲያውቀው የሚፈልጉትን እውነታ በቀጥታ የሚያውቅ ሰው ማለት ነው።

   ምስክሮችዎ ወደ ችሎቱ መደወል እንዲችሉ ከችሎቱ ማስታወቂያ ላይ ቀኑን፣ ሰዓቱን፣ ስልክ ቁጥር እና የመዳረሻ ኮድ ይስጧቸው

## ሰነዶችን ማስገባት (ኤግዚቢቶች)

ዳኛው ማግኘት የሚችሉት ለችሎቱ ወደ OAH የሚላኩትን የኤግዚቢት ቅጂዎች እና ሌሎች ሰነዶችን ብቻ ነው።

ዳኛው እንዲያዩዋቸው የሚፈልጓቸው ተጨማሪ ሰነዶች ካሉዎት ወደ OAH **እና በችሎት ማስታወቂያ ውስጥ ለተዘረዘሩት ሌሎች ወገኖች በሙሉ ወዲያውኑ መላክ አለብዎት።**

ሰነዶችን በሚከተለው ያስገቡ፦

- ድር ጣቢያ፦ ሰነዶችን በተሳታፊ ፖርታል ላይ ወደ ጉዳይዎ ይስቀሉ (ለመመሪያዎች ሣጥንን ይመልከቱ)።
- ደብዳቤ፦ 16201 E. Indiana Avenue, Suite 3000
  Spokane Valley፣ WA 99216
- ፋክስ፦ (509) 456-3980

**የፋይል መጠን ገደቦች።** የተሳታፊ ፖርታል ላይ የተሰቀሉ ሰነዶች በአንድ ፋይል ከ1 ጊጋባይት መብለጥ የለባቸውም። ወደ OAH (USB ፍላሽ ድራይቭ) የሚላኩ የኤሌክትሮኒክ ፋይሎች በአንድ ፋይል ከ2 ጊጋባይት መብለጥ የለባቸውም።

በOAH የተሳታፊ ፖርታል በመስመር ላይ ወይም በCD፣ DVD ወይም ፍላሽ አንጻፊ ላይ በደብዳቤ **የቪድዮ ወይም የኦዲዮ ኤግዚቢቶችን** ያስገቡ (እነዚህ ወደ እርስዎ አይመለሱም)። የፋይሉ ዓይነት MP3 ወይም MP4 መሆን አለበት።

**የእርስዎን ኤግዚቢቶች ለማስገባት አይጠብቁ።** ከችሎትዎ በፊት ከሁለት የሥራ ቀናት ቀደም ብለው (48 ሰዓታት፣ የሳምንቱ የመጨረሻ ቀናትን እና በዓላትን ሳይጨምር) ለOAH እና ለሁሉም ወገኖች ያቅርቧቸው።

**OAH ለእርስዎ ሰነዶችን ወደ ሌሎች ወገኖች አይልክልዎም። ይህን እራስዎ ማድረግ አለብዎት።** ሰነዶችዎ ለOAH እና ለሌሎች ወገኖች አስቀድመው ካልቀረቡ፣ ሰነዶችዎ ላይታዩ ይችላሉ።

**OAHን በመጠቀም የተሳታፊ ፖርታል**

የጉዳይዎን ኤሌክትሮኒክ መዳረሻ ለማግኘት የOAHን ድር ጣቢያን www.oah.wa.gov ላይ መጎብኘት ይችላሉ። ዳኛው እንዲያዩዋቸው የሚፈልጓቸውን ሰነዶች ለማቅረብ እና ከችሎቱ በፊት በጉዳይዎ ውስጥ ያሉትን ሰነዶች ለማንበብ ፖርታሉን መጠቀም ይችላሉ። ሰነዶች ወደ ፋይሉ ሲታከሉ ማሳወቂያ አይደርስዎትም።

መለያ ለመፍጠር እና ጉዳይዎን ለመድረስ መመሪያዎች በችሎት ጥቅልዎ የሽፋን ገፅ ላይ አሉ። በድር ጣቢያው ላይ ወይም ሰነዶችን ለመስቀል ችግር ካጋጠመዎ እገዛ ለማግኘት ወደ **(800) 366-0955** ይደውሉ።

ሰነዶችን ወደ OAH እና ሌሎች ወገኖች ከመላክዎ በፊት ሚስጥራዊ መረጃዎችን (ለምሳሌ የማህበራዊ ዋስትና ቁጥሮች፣ የባንክ ሂሳብ ቁጥሮች እና የመንጃ ፈቃድ ቁጥሮች) ያስወግዱ።

**የእርስዎን ጉዳይ በመመርመር ላይ**

የእርስዎ ጉዳይ የሚመለከቱትን ህጎች ለመመርመር ፍላጎት ካለዎት የተሻሻለው የWashington ኮድ (Revised Code of Washington, RCW) እና የWashington አስተዳደራዊ ህግ (Washington Administrative Code, WAC) www.oah.wa.gov ላይ ይገኛሉ።

ለስራ አጥ ሰራተኞች የESD *መመሪያ መጽሐፍ* ስለ ጥቅማጥቅሞች መረጃ ይሰጣል። በመመሪያው ውስጥ ያለውን መረጃ የመረዳት ሃላፊነት አለብዎት። ከችሎትዎ በፊት መመሪያውን እንዲያነቡ እንመክርዎታለን።

የESD *መመሪያ መጽሐፍ* በESD ድር ጣቢያ ላይ ይገኛል። የESD ድር ጣቢያ በስፓኒሽኛ ይገኛል እንዲሁም በ16 ሌሎች ቋንቋዎች የተወሰነ መረጃ አለው። ነፃ የቃል አስተርጓሚ ከፈለጉ ወይም ጥያቄዎች ካሉዎት በ 1-800-318-6022 ወደ ESD ይደውሉ።

## ችሎት ላይ ምን ይከናወናል?

ችሎትዎ አጭር ቢሆንም እስከ ሁለት ሰዓታት ድረስ ሊወስድ ይችላል። ከብዙ ይግባኝኞች፣ ምስክሮች፣ ወይም የቃል አስተርጓሚ ጋር የሚደረጉ ችሎቶች በአጠቃላይ ከሌሎች ችሎቶች የበለጠ ጊዜ ይወስዳሉ።

**ጸጥ ያለ ቦታ እና ጥሩ የስልክ ግንኙነት ሊኖርዎት ይገባል። ከበስተጀርባ ያለ ጫጫታ በችሎቱ ቀረጻ ላይ ጣልቃ ሊገባ ይችላል። የድምጽ ማውጫ ስልክ ወይም የብሉቱዝ ጆሮ ማዳመጫዎችን መጠቀም ያለብዎት የድምፅ ጥራቱ ጥሩ እና ያልተዛባ መሆኑን ካረጋገጡ ብቻ ነው።**

ችሎቱ ሲጀመር ዳኛው ጉዳዩን እና የችሎቱን ሂደት ይገልፃሉ። ዳኛው ሁሉም ሰው እራሳቸውን እንዲገልጹ ይጠይቃሉ። ችሎቱ ይቀዳል።

ዳኛው እያንዳንዱ ሰው መቼ ማውራት እንዳለባቸው ይወስናሉ። ዳኛው ጥያቄዎችን (ከዚህ በታች ይመልከቱ) የሚጠይቁ ሲሆን ማን በችሎቱ ጊዜ ጥያቄዎችን የመጠየቅ እድል እንደሚኖረው ያብራራሉ።

ሁሉም ወገኖች የታሪኩን የራሳቸውን ክፍል የመናገር እድል ይኖራቸዋል።

ዳኛው በምስክርነቱ እና በሰነዶቹ ላይ ተመስርተው የጽሑፍ ውሳኔ ይሰጣሉ። ውሳኔው ወደ

የተሳታፊ ፖርታል ይሰቀላል። ውሳኔውን በደብዳቤ ለመቀበል መምረጥ ይችላሉ።

ችሎቱ ታሪክዎን ለመንገር እና ሰነዶችዎን ለማጋራት ብቸኛው እድልዎ ነው። ችሎት እንዲኖር ከጠየቁ ነገር ግን በዛ ላይ ካልተሳተፉ፣ የእርስዎ የችሎት ጥያቄ ውድቅ የሚሆን ሲሆን የESD ውሳኔ ተግባራዊ ይሆናል።

በዳኛው ውሳኔ ካልተስማሙ፣ በESD ውስጥ ለኮሚሽነሩ የግምገማ ቢሮ ይግባኝ የማቅረብ መብት አለዎት። የጽሑፍ ውሳኔው መመሪያዎችን እና የይግባኝ ቀነ ገደብን ያካትታል።

**የችሎቱን የቪድዮ ምሳሌ (በእንግሊዘኛ እና በስፓኒሽ) እና ተጨማሪ በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን ጨምሮ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የእኛን ድር ጣቢያ የሚከተለው ላይ ይጎብኙ**

**www.oah.wa.gov**

**ማንኛቸውም ጥያቄዎች ካሉዎት፣ ወደ፡- (800) 366-0955 ይደውሉ**

## በችሎቱ ላይ ዳኛው ሊጠይቋቸው የሚችሏቸው ጥያቄዎች

ከጉዳይዎ ጋር ተያያዥ ከሆኑ እነዚህን ጥያቄዎች በችሎትዎ ላይ ለመመለስ ዝግጁ ይሁኑ።

በሁሉም ሁኔታዎች፣ እርስዎ የይገባኛል ጥያቄ አቅራቢ ከሆኑ፡-

- ለስራ አጥነት ጥቅማጥቅሞች ሳምንታዊ ጥያቄዎችን መቼ ማስገባት ጀመሩ?
- ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄዎችን መቼ ማስገባት አቆሙ?
- ሳምንታዊ የይገባኛል ጥያቄዎችን በሚያስገቡበት ጊዜ፣ እርስዎ፡-
    - አካላዊ ሁኔታዎ ስራ መሥራት የሚያስችል ነበር?
    - በጊዜዎ ላይ ምንም ገደብ ሳይኖር ለሥራ መገኘት ይችሉ ነበር?
    - ሥራን በንቃት እየፈለጉ ነበር?
- መሥራት ካልቻሉ ወይም ለሥራ ካልተገኙ፣ ለመሥራት ያልቻሉት ወይም በሥራ ላይ የማይገኙበት የትኞቹ ቀናት ወይም ሰዓቶች ናቸው?
- በእነዚያ ቀናት ወይም ሰዓቶች ላይ መሥራት ያልቻሉት ወይም ለሥራ ያልተገኙት ለምንድን ነበር?
- ሥራ እየፈለጉ ካልነበረ፣ ምክንያቱ ምንድን ነው?

ጉዳይዎ የሥራ ማብቃትን የሚያካትት ከሆነ (ሥራ መቆም፣መባረር ወይም ለጊዜው ከሥራ ላይ መቀነስ)

- የሥራ ቅጥሩ መጀመሪያ እና ማብቂያ ቀናት የትኞቹ ነበሩ?
- የሥራ ቅጥሩ እንዴት አበቃ?
- የይገባኛል ጥያቄ አቅራቢ ከሆኑ እና ሥራዎን ካቆሙ፣ ያቆሙበት ምክንያት ምንድን ነው?
- ቀጣሪ ከሆኑ እና የይገባኛል ጥያቄ አቅራቢውን ከሥራ ካባረሩ፣ የይገባኛል ጥያቄ አቅራቢውን ከሥራ ያባረሩበት ምክንያተ ምንድን ነው?

የሆነ ዓይነት ገቢ ለመቀበል ጥቅማጥቅሞች በተቀነሱባቸው ሁኔታዎች፡-

- ለሥራ አጥነት ጥቅማጥቅሞች በየሳምንቱ ላቀረቡት የይገባኛል ጥያቄ ለእያንዳንዱ ሳምንት ያገኙት ወይም የተከፈለዎት ትክክለኛ መጠን ምን ያህል ነበር?
- *እነዚህን መጠኖች የሚያሳዩ የክፍያ ማከማቻዎችን ወይም ሌሎች ሰነዶችን ይሰብስቡ። በገፅ 2 ላይ ያሉትን መመሪያዎች በመጠቀም ከችሎቱ ቀን በፊት ለዳኛው እና ለሌሎች ወገኖች ሊያቀርቧቸው ይችላሉ።*

ከመጠን ያለፈ ክፍያን ለማስቀረት ጥያቄዎን በሚያካትቱ ጉዳዮች ላይ፡-

- ለሁሉም የቤተሰብዎ አባላት ዝርዝር ወርሃዊ ወጪዎች እና ገቢዎች ምን ያህል ናቸው?
- ምን ዓይነት ዕዳዎች እና ንብረቶች አሉዎት?
- ከመጠን ያለፈ ክፍያን ለመክፈል የፋይናንስ ችግር የሚያደርገው ሌላ ነገር አለ?
- *ለዳኛው ትክክለኛ እና የተሟላ መረጃ ለመስጠት ለችሎትዎ የተዘጋጁ ማስታወሻዎች ወይም ሰነዶች ይኑሩዎት።*

| እራስዎን መወከል ወይም ነፃ የህግ እርዳታ ለማግኘት መደወል ይችላሉ። |
|---|

## ውክልና

በችሎትዎ ላይ እራስዎን መወከል ይችላሉ ወይም ሌላ ሰው እንዲወክልዎ መጠየቅ ይችላሉ።
አብዛኞቹ በስራ አጥነት ችሎቶች ላይ የሚሳተፉ ሰዎች እራሳቸውን ይወክላሉ።

የችሎት ሂደቱ የተነደፈው ሰዎች እራሳቸውን እንዲወክሉ ለማስቻል ነው።

ሌላ ሰው የሚወክልዎ ከሆነ፣ ህጋዊ እና የአሰራር ጥያቄዎችን ይመልሳሉ እንዲሁም ህጋዊ ክርክሮችን ለእርስዎ ይከራከሩልዎታል። ተወካይዎ በእርስዎ ቦታ ሊመሰክሩ እና ለማንም ሰው ማስተርጎም አይችሉም።

የእርስዎ ተወካይ ግዴታ ጠበቃ መሆን የለባቸውም። ጓደኛ ወይም የቤተሰብ አባል ሊወክሉዎት ይችላሉ።

ጠበቃ መቅጠርም ይችላሉ። ያንን ጠበቃ ራስዎ መቅጠር አለብዎት። ግዛቱ ለጠበቃዎ የሚከፈል ክፍያን አይከፍልም።

## መርጃዎች

አንዳንድ ድርጅቶች ነፃ ወይም ዝቅተኛ ወጪ ያላቸው የሕግ አገልግሎቶች ይሰጣሉ።
ፍላጎት ካለዎት፣ ለእርዳታ ሊያነጋግሯቸው የሚችላቸው አንዳንድ መርጃዎች እዚህ አሉ፦

| የመርጃ ስም | ስልክ ቁጥር | ድር ጣቢያ |
|---|---|---|
| የስራ አጥነት ህግ ፕሮጀክት<br><br>(ነፃ የሕግ ውክልና። ነፃ አስተርጓሚዎች ቀርበዋል) | (888) 441-9178<br><br>ኢሜይል፦ info@ulproject.org | https://unemploymentlawproject.org |
| የተቀናጀ የህግ ትምህርት፣ ምክር እና ሪፈራል (Coordinated Legal Eduction, Advice and Referal, CLEAR) የሰሜን ምዕራብ ፍትህ ፕሮጀክት (Northwest Justice Project) | (888) 201-1014 | https://www.washingtonlawhelp.org |
| የWashington ግዛት ባር ማህበር | (800) 945-9722 | https://www.wsba.org/for-the-public/find-legal-help |